የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፳፭ አዲስ አበባ የካቲት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No.25
ADDIS ABABA 3rd,March , 2025

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፭፻፷፯/፪ሺ፲፯

የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ግሩፕ ማቋቋሚያ ደንብ ......................................ገጽ ፲፯ሺ፯፻፲፭

**Content**

Regulation No.567/2025

Defense Engineering Industry Group Establishment Regulation ……..……………………......Page 17715

## ደንብ ቁጥር ፭፻፷፯/፪ሺ፲፯

## የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ግሩፕ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፬/፪ሺ፲፮ አንቀፅ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና አንቀፅ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የመከላከያ ኢንጂነሪን ግ ኢንዱስትሪ ግሩፕ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፭፻፷፯/፪ሺ፲፯ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡"

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ ያሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ :-

## REGULATION No. 567/2025

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION FOR THE ESTABLISHMENT OF DEFENSE ENGINEERING INDUSTRY GROUP

The Council of Ministers has issued this regulation in accordance with Article 6 Sub-Article (1) and Sub-Article (1) of Article 47 of the State-Owned Enterprises Proclamation No. 1314/2024.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Defense Engineering Industry Group Establishment Regulation No. 567/2025."

### 2. Definitions

In this regulation, unless the context otherwise requires:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 438.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

Generated by CamScanner from intsig.com

፩/ **"ወታደራዊ ምርቶች"** ማለት ለመከላከያና ለፀጥታ ኃይሎች የሚያገለግሉ ቀላል፣ መካከለኛና ከባድ የጦር መሳሪያዎች፣ የተለያዩ የአጭር፣ መካከለኛና ረጅም ርቀት ተተኳሾች፣ ፈንጂዎች፣ ወታደራዊ ምርት ማምረቻ የሚውሉ ኬሚካሎችና ግብአቶች ፣ የውጊያ ተሽከርካሪዎች፣ ብረት ለበሶች፣ ታንኮች፣ አውሮፕላኖች፣ ሄሊኮፕተሮች፣ ድሮውኖች፣ የኤሌክትሮኒክስና ኦፕትሮኒክስ ውጤቶች፣ ለቅኝት ፣ ለተኩስ መምሪያና መቆጣጠሪያ የሚውሉ መሳሪያዎች፣ ወታደራዊ ሬዲዮኖች እና የተለያዩ አባሪና መለዋወጫ ዕቃዎች እንዲሁም የፀጥታ አካላት ደህንነት መጠበቂያ ትጥቆች ነው፡፡

፪/ **"ሲቪል ምርቶች"** ማለት ከወታደራዊ ምርቶች በተጓዳኝ ለሲቪል ስራ የሚያገለግሉ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች፣ የማምረቻ ማሽን፣ መለዋወጫና አባሪ ዕቃዎች፣ ኮምፖዛይት፣ የኤሌክትሮኒክስና ኤሌክትሮ መካኒካል ውጤቶች፣ ለግንባታና ለመንገድ ሥራ የሚያገለግሉ ድማሚቶች ነው፡፡

**፫. <u>መቋቋም</u>**

፩/ መከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ግሩፕ ከዚህ በኋላ "ግሩፕ" እየተባለ የሚጠራ በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ግሩፑ በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፬/፪ሺ፲፮ መሰረት ይተዳደራል፡፡

**፬. <u>ተቆጣጣሪ ባለስልጣን</u>**

የግሩፑ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

**፭. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>**

የግሩፑ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ወይም ወኪል ሊኖረው ይችላል፡፡

1/ **"Military products"** means light, medium and heavy weapons used for defense and security forces, various short, medium and long-range ammunitions, explosives, chemicals and inputs used in the manufacture of military products, ironclad vehicles, armored vehicle, tanks, aircraft, helicopters, drones, electronic and optronics products, communication radios with respective accessories and spare parts used for defense and security forces.

2/ "Civil products" means various vehicles, production machinery, spare parts and attachment materials, composites, electronic and electromechanical products, dummies used for construction and road work in conjunction with military products.

**3. <u>Establishment</u>**

1/ The Defense Engineering Industry Group (hereinafter referred to as the "Group") is hereby established as a Federal Government owned enterprise.

2/ The Group shall be administered in accordance with the Federal Government-owned Enterprises Proclamation No. 1314/2024.

**4. <u>Supervising Authority</u>**

The supervising authority of the group shall be the FDRE Ministry of Defense.

**5. <u>Head Office</u>**

The Group is headquartered in Addis Ababa and may have a branch or agent elsewhere as needed.

Generated by CamScanner from intsig.com

**፮. ዓላማ**

ግሩፑ የተቋቋመባቸው አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ የመከላከያን የአሁንና የወደፊት ወትሮ ዝግጁነት ሊያረጋግጡ የሚችሉ ወታደራዊ ምርቶችን በጥራት አምርቶ ማቅረብ፣

፪/ ለወታደራዊና በተዛማጅ ለሲቪል አገልግሎት የሚውሉ ምርቶችን የዲዛይን፣ የማምረት፣ የመፈተሽ፣ የመጠገን፣ ማደስ፣ ማዘመንና ማሻሻል እንዲሁም ወታደራዊ ምርት ማምረቻ ፋብሪካዎችን መትከልና ኮሚሽን በማድረግ ወደ ምርት ሂደት ማስገባት፣

፫/ ወታደራዊ እና ተያያዥ የሲቪል ቴክኖሎጂዎችን የመመራመርና ማልማት ስራ መስራት፣

፬/ በግሩፑ የሚመረቱ ምርቶችን ከሀገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ ኤክስፖርት ማድረግ፣

፭/ የግሩፑን ተልዕኮ ለማሳካት ወደ ገበያ ለመውጣትና ተወዳዳሪ ለመሆን በሚያስችሉ ተግባራት ላይ በሀገር ውስጥ ወይም የውጪ ኩባንያዎች ጋር በሽርክና መስራት፣

፮/ ከሀገሪቱ የመከላከያ ኃይል ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ አንፃር በመንግስት ውሳኔና በጀት ሊሰሩ የሚችሉ ወቅታዊና ለሀገር ደህንነት ጠቀሜታ ያላቸውን የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታዎችን ማከናወን፣

፯/ እንደአስፈላጊነቱ የፍላጎትና አቅርቦት ክፍተት ሲኖር እና በተቆጣጣሪው ባለስልጣን ሲፈቀድ ወታደራዊ ምርቶችን ከውጪ አስገብቶ ለገበያ ማቅረብ፣

፰/ ሚስጢራዊነታቸው በከፍተኛ ደረጃ ተጠብቆ መታተም ያለባቸውን ወታደራዊ፣ የፀጥታና ደህንነት እንዲሁም ማናቸውም መንግስታዊና የግል ተቋማት ዲጂታልና መደበኛ ሰነዶች፣ መፅሔቶችና የመሳሰሉት ዶክመንቶች ሕትመት ማከናወን፣

**6. Objectives**

The Group shall have the following objectives:

1/ Produce and deliver quality military products that can ensure the current and future readiness of defense;

2/ Designing, manufacturing, testing, repairing, refurbishing, updating and improving products for military and related civilian use, as well as installing and commissioning military product manufacturing factories and putting them into production;

3/ Conduct research and development of military and related civil technologies;

4/ Export products produced by the Group beyond domestic consumption;

5/ Work in partnership with local or foreign companies on activities that enable the group to go out to the market and become competitive in order to achieve the Group's mission;

6/ Carry out timely and technological capacity buildings that can be carried out at the discretion and budget of the Government in view of the strategic importance of the country's defense forces;

7/ Import and market military products when there is a demand and supply gap as necessary and when approved by the supervising authority;

8/ Carry out the publication of military, secured and trustworthy and any public and private institutions' digital and regular documents, magazines and similar documents whose confidentiality must be maintained at the highest level ;

Generated by CamScanner from intsig.com

፱/ የገንዘብ ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያ መሰረት በማድረግ በተቆጣጣሪ ባለስልጣን በሚሰጠው የፖሊሲ አቅጣጫ መሰረት ቦንድ መሸጥ፣ መግዛት፣ በዋስትና ማስያዝ፤

፲/ የፋይናንስ አቅሙን በመገምገም በተቆጣጣሪው ባለስልጣን ሲፈቀድ ከአላማው ጋር ተዛማጅ በሆኑ ኢንቨስትመንቶች ላይ ሼር በመግዛት መሳተፍ፤

፲፩/ ተጠሪ ለሆነበት ተቋም በሕግ ሚስጢር ተብለው የተቀመጡና ግሩፑን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ማክበርና መተግበር፤

፲፪/ የግሩፑ ተቋማት በሚገኙበት ቦታ ለሕብረተሰቡ የማህበራዊ ኃላፊነት ተግባራትን መወጣት የሚያስችሉ ግልጋሎቶችን መስጠት፤

፲፫/ ተልዕኮውን ለማሳካት የሚረዱ ተቀፅላዎችን ማቋቋም እንዲሁም በስሩ ያሉ ተቀፅላዎች የሕግ ሰውነት ኖሯቸው እንዲቋቋሙ ሊያደርግ ይችላል፤

፲፬/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ስራዎችን መስራት፡፡

## ፯. <u>የተፈቀደ ካፒታል</u>

ለግሩፑ የተፈቀደው የካፒታል መጠን ብር ፳፱ ቢሊዮን ፮፻፹ ሚሊዮን ፫፻፶፱ሺህ ፩፻፵፬ ብር ከ፰ ሳንቲም(ሀያ ዘጠኝ ቢሊየን ስድስት መቶ ሰማኒያ ሚሊዮን ሦስት መቶ አምሳ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ አርባ አራት ብር ከስምንት ሳንቲም) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፯ ቢሊዮን ፬፻፳ ሚሊዮን ፹፱ሺህ ፯፻፹፮ ብር ከ፪ ሳንቲም (ሰባት ቢሊዮን አራት መቶ ሀያ ሚሊዮን ሰማኒያ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሰማኒያ ስድስት ብር ከሁለት ሳንቲም) በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል፡፡

## ፰. <u>ኃላፊነት</u>

ግሩፑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

9/ Based on the guidelines issued by the Ministry of Finance, Selling, buying and guaranteeing bonds according to the policy direction given by the regulatory authority;

10/ By assessing its financial capabilities participate in investments by purchasing shares that are related to its objectives when approved by the supervising authority;

11/ Respect and implement matters that are classified as confidential by law to the supervising authority that concerns the group;

12/ Providing social services to the community where the Group's institutions are located;

13/ Form a subsidiary as well as let its subsidiaries to be an independent legal body under its undertakings;

14/ To engage in other related activities necessary for the attainment of its purpose.

## 7. <u>Authorized Capital</u>

The authorized capital of the group shall be birr 29,680,359,144.08 (twenty nine Billion six hundred eighty million three hundred fifty nine thousand one hundred forty four birr and 08 cents ) of which birr 7,420,089,786.02(seven billion four hundred twenty million eighty nine thousand seven hundred eighty six birr and 02 cents) is paid up in cash and in kind.

## 8. <u>Liability</u>

The group shall not be liable beyond its total assets.

Generated by CamScanner from intsig.com

**፱. የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

፩/ በመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፷፬/፪ሺ.፲፪ ተቋቁሞ የነበረው የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን መብትና ግዴታዎች እንዲሁም አዲስ የተቋቋመው ኤሌክትሮኒክስ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለግሩፑ ተላልፈዋል፡፡

፪/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፩/፩ሺ.፱፻፹፮ ተቋቁሞ የነበረው የብራና ማተሚያ ድርጅት መብትና ግዴታ በዚህ ደንብ ለግሩፑ ተላልፏል፡፡

፫/ በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ማቋቋሚያ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፸፭/፪ሺ.፲፫ መሰረት በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ስር የነበሩት የቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ እና ኤሌክትሮኒክስ ኢኩፕመንት ማምረቻ ኢንዱስትሪ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለግሩፑ ተላልፏል፡፡

**፲. የተሻሩ ደንቦች**

፩/ የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፷፬/፪ሺ.፲፪ እንደተሻሻለ በዚህ ደንብ ተሽሯል፤

፪/ የብራና ማተሚያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፩/፩ሺ.፱፻፹፮ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

**፲፩. ግሩፑ የሚቆይበት ጊዜ**

ግሩፑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

**9. Transfer of Rights and Obligations**

1/ The right and obligations of defense engineering Industry Corporation established by the council of minister No.464/2020 and newly established electronics engineering industry have been transferred to the group in accordance with this regulation.

2/ The right and obligation of `Brana` printing company established by council of ministers regulation No. 171/1994 have been transferred to the group in accordance with this regulation.

3/ According to the council of ministers regulation No.475/2020 the establishment of ethio-engineering group, the right and obligation of Bishoftu automotive manufacturing industry and electronics equipment manufacturing industries which was under the auspices of Ethio-engineering group have been transferred to the group in accordance with this regulation.

**10. Repealed Regulations**

1/ Defense engineering Industry Corporation establishment regulation council of minister regulation No.464/2020 repealed as amended.

2/ Brana printing company establishment regulation council of ministers regulation No. 171/1994 repealed.

**11. Duration**

The group established for an indefinite duration.

Generated by CamScanner from intsig.com

፲፪. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፯

አብይ አህመድ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

12. Effective Date

This regulation shall enter in to force on the date of its publication in the Federal Negarit gazette.

Done at Addis Ababa, this 3rd day of March , 2025

ABIY AHMED (DR)

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

Generated by CamScanner from intsig.com